# የመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010ን ለማሻሻል
## ስለተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ የቀረበ አጭር መግለጫ

## 1. መግቢያ

የመንግሥት እና የግል አጋርነት (መግአ) አሰራር በሀገራችን ተግባራዊ እንዲደረግ ለማስቻል የመግአ ፖሊሲ ነሐሴ 2009 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተመርምሮ ከፀደቀ በኋላ ፖሊሲውን ለማስፈጸም የመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1076/2010) በየካቲት ወር 2010 ዓም ጸድቆ በስራ ላይ መዋሉ ይታወቃል። የመግአ አሰራር በዋናነት የግል ሴክተሩን እውቀት፤ ክህሎት እና የፋይናንስ አቅም በመጠቀም የሕዝብ አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶችን ጥራት እና ደረጃ ለማሳደግና ለማስፋፋት፤ ስራው በግልጽ ውድድርና ፍትሐዊነት እንዲፈጸም ለማድረግ እንዲሁም በሀገራችን ማክሮ ኢኮኖሚ ሂደት የሚታዩ ተግዳሮቶችን ማለትም የውጭ ዕዳ ጫና ለመቀነስ እና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግርን እንዲታደግ ለማድረግ እንደ አንድ የልማት ፋይናንስ አማራጭ ዘዴ በመውሰድ የተቀየሰ የሕግ ማዕቀፍ ነው። የመግአ አሰራር በሕጉ መሰረት በማዕከል ደረጃ በገንዘብ ሚኒስቴር ስር በተቋቋመ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ጽ/ቤት አስተባባሪነት የሚተገበር ነው።

የመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚተገበሩ የመንግሥት እና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚነት ያለው ሲሆን ነገር ግን ይህ አዋጅ በነዳጅ፤ ማዕድን፤ ሚኒራል፤ የአየር ክልል ሙብት እና የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወይም በመንግሥት ባለቤትነት ስር ያለን መሰረተ ልማት እና ወደ ግል ማዛወር ወይም ሽያጭ ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

## 2. የማሻሻያው አስፈላጊነት

የመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ ከመንግሥት ጋር በአጋርነት የሚሰራውን የግል ባለሀብት ለመምረጥ የሚያስችሉ የተለያዩ የጨረታ ዘዴዎችን ይከተላል። ከእነዚህም ዘዴዎች መካከል በዋነኛነት ተፈፃሚ የሚደረገው የግልጽ ጨረታ ዘዴ ሂደት ሲሆን በተጨማሪም ሌሎች አማራጭ የጨረታ ዘዴዎችም በአዋጁ ተካተው ይገኛሉ። ከእነዚህም አማራጭ የጨረታ ዘዴዎች መካከል በአዋጁ አንቀጽ 39 እና 40 ላይ ተደንግጎ የምናገኘው የቀጥተኛ ድርድር (Direct Negotiation) ዘዴ አንዱ ሲሆን ይህንንም ዘዴ ለመጠቀም የሚያስችሉ በሕጉ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች እና ድርድሩ የሚካሄድበት የሥነ-ሥርዓት ሂደት በሕጉ ተደንግጎ ይገኛል። በአዋጁ አንቀጽ 39(1) ላይ እንደተቀመጠው በገንዘብ ሚኒስቴር ስር የሚገኘው የመንግሥት እና የግል አጋርነት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የቀጥታ ድርድሩን ማድረግ የሚችለው በመጀመሪያ የፕሮጀክት ሀሳቡ ለዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ ሲቀርብለት እና በመግአ ቦርድ ሲጸድቅ እንዲሁም የፕሮጀክት ሀሳቡ በአንቀጹ ከ ሀ እስከ ረ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱን አሟልቶ ሲገኝ ነው።

የመግአ አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ እስካሁን ካጋጠሙ የአፈጻጸም ተግዳሮቶች አንፃር ሲታይ የመግአ አጠቃላይ የጨረታ አሰራር ሂደት ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድ መሆኑ ተረጋግጧል። በሌላ በኩል መንግሥት የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት የያዘውን የሪፎርም ስራ ፈጥኖ መተግበርን ይጠይቃል። በዚህም መሰረት በርካታ ጠቃሚ ፕሮጀክቶች በመግአ በቀጥታ ድርድር እንዲተገበሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር እየቀረቡ ቢሆንም ፕሮጀክቶቹ የሚቀርቡበት መንገድ በአዋጁ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ስለማያሟላ ከግል ባለሀብቱ ጋር የቀጥታ ድርድር በማድረግ ለመተግበር አልተቻለም። በመሆኑም በተመረጡ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች የሕዝብ ፍላጎትን ለማሟላት እንዲቻል በመንግሥት ሲወሰን ከተለያዩ የውጭ ሀገራት

መንግሥታት በሁለትዮሽ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ግንኙነት አማካኝነት እንዲሁም ከውጭ ባለሀብቶች ጋር በሚደረግ ግንኙነትና በተደረሰ መግባባት መሰረት ለአገር እና ሕዝብ ጠቀሜታ ያላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦችን በቀጥታ ድርድር መተግበር ጠቃሚ መሆኑ ታምኖበታል። ነገር ግን አሁን በስራ ላይ ያለው አዋጅ ይህን አሰራር የማይፈቅድ በመሆኑ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል።

3. __የማሻሻያው ይዘት__

የማሻሻያ አዋጁ አስቀድሞ በአዋጁ ከተቀመጡት የፕሮጀክት ሀሳብ አቅራቢው የግል ባለሀብት ጋር ለሚደረግ የቀጥታ ድርድር ቅድመ-ሁኔታዎች በተጨማሪ መንግሥት ለመንግሥት የሚኖረውን የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ግንኙነት ወይም አቅም ያለው የግል ኩባንያ ከመንግሥት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት መሰረት በማድረግ የፕሮጀክት ሀሳቡ አገራዊ ጠቀሜታ እንዳለው ሲታመንበት ከግል ባለሀብቱ ጋር በሚደረግ የቀጥታ ድርድር በመግአ እንዲተገበር እንዲፈቅድ ለመግአ ቦርድ ይቀርባል። እንዲሁም ኩባንያው ወይም በኩባንያው የቀረበው የፕሮጀክት ሀሳብ ማሟላት የሚገባቸውን ዝቅተኛ መመዘኛዎችን የሚያስቀምጥ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ አስቀድሞ በአዋጁ የቀጥታ ድርድር ከሚመራባቸው ሥነ-ሥርዓቶች በተለየ መልኩ ለዚሁ ዓላማ ማስፈጸሚያ የሚሆን ስለፕሮጀክት ሀሳቡ አቀራረብ፤ ጥናት እና ድርድር ሂደት የሚወስኑ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች በማሻሻያ አዋጁ ተካተዋል።

ስለሆነም የመንግሥት ለመንግሥት ባለው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ግንኙነት አማካኝነት ወይም በመንግሥት በልዩ ሁኔታ በግል ባለሀብቶች እንዲለሙ የሚፈለጉ የፕሮጀክተ ሀሳቦች ለመንግሥት ቀርበውና ዝርዝር ጥናት ተደርጎባቸው በመግአ ቦርድ ሲወሰን በቀጥታ ድርድር መተግበር እንዲቻል ለማድረግ የተዘጋጀው የመንግሥት እና የግል አጋርነት ማሻሻያ አዋጅ ረቂቅ በምክር ቤቱ ታይቶ ይፀድቅ ዘንድ ይህ አጭር መግለጫ ቀርቧል።